Women's Health Needs STUDY



# የሴቶች የጤና ፍላጎቶች ጥናት (WHNS)

WHNS ስለ ሴቶች የጤና እንክብካቤ ልምዶች እና ፍላጎቶች እንዲሁም ስለሴት ልጅ ግርዛት (FGM/C) መረጃን የሰበሰበ **የአንድ ጊዜ ጥናት ነው።**

ጥናቱ የተካሄደው **ከህዳር 2020 እስከ ሰኔ 2021** በ ዩናይትድ ስቴትስ ባሉት አራት የሜትሮፖሊታን አካባቢዎች **(አትላንታ፣ ሚኒያፖሊስ፣ ኒው ዮርክ እና ዋሽንግተን፣ ዲሲ ነው)** ።

## ጥናቱ ላይ ለመሳተፍ ብቁነት

ከ 18 እስከ 49 ዓመት የሆኑ **ሴቶች**

\+

**የሴት ልጅ ግርዛት የተለመደ በሆነበት አገር** የተወለደች እናት

\+

**አንዱን** የጥናት ቋንቋ የምትናገር

## በጥናቱ ውስጥ የተሳተፉ

**1,132 ሴቶች**

### እድሜ ክልል

| | | |
|---|---|---|
| 31% | 38% | 31% |
| **18-29** አመት | ከ**30-39** አመት | ከ**40-49** አመት |

### የትምህርት ደረጃ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 15% | 22% | 33% | 30% |
| ከሁለተኛ ደረጃ/ GED[ሀ] ዲፕሎማ ያነሰ | ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት / GED ዲፕሎማ | ኮሌጅ/ አሶሺየት ዲግሪ | የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ |

### የስደት ሁኔታ

| | | |
|---|---|---|
| 87% | 10% | 3% |
| 1.0 ትውልድ፤ በ13 አመታቸው ወይም ከዚያ በላይ ሆነው ወደ አሜሪካ የተሰደዱ | 1.5 ትውልድ፤ ከ13 አመታቸው በፊት ወደ አሜሪካ የተሰደዱ | 2.0 ትውልድ፤ በአሜሪካ የተወለዱ. |

### የጋብቻ ሁኔታ

| | | |
|---|---|---|
| 61% | 14% | 25% |
| ያገባች/ከአጋር ጋር የምትኖር | ቀደም ሲልአግብታ የምታውቅ | በጭራሽያላገባች/ከአጋር ጋር ኖራ የማታውቅ |

[ሀ] አጠቃላይ የትምህርት ልማት



# በጥናቱ ውስጥ የተሳተፉ

**1,132 ሴቶች**

## የትውልድ ቦታ ^ *




^ የሴቷ ወይም የእናትየው ትውልድ ቦታ ጥናቱ በሚፈቅደው ቦታ ካልሆነ።
^ ምዕራብ አፍሪካ ቡርኪናፋሶ፣ ጋምቢያ፣ ጊኒ፣ ማሊ፣ ሞሪታኒያ እና ሴራሊዮን ይገኙበታል።
* የትውልድ አገር ካርታ በ© GeoNames፣ Microsoft፣ OpenStreetMap፣ TomTom የተጎለበተ

# በጥናቱ ውስጥ ለሁሉም ሴቶች የጤና እንክብካቤ ማግኘት

## የጤና ኢንሹራንስ ሽፋን

**ከግማሽ በላይ (52%)** ሜዲኬይድ ነበራቸው።




## አስተርጓሚ

**27%** የሚሆኑት የጤና እንክብካቤ አቅራቢቸውን ሲጎበኙ አ አስተርጓሚ ይመርጣሉ።

አስተርጓሚ ከሚመርጡ ሴቶች መካከል፣ **ከ3ቱ (66%) 2** የሚሆኑት በመጨረሻ ጉብኝታቸው ወቅት አንድ ተሰጥቷቸዋል።



# የስነ ተዋልዶ ጤና

በዳሰሳ ጥናቱ ከተሳተፉ ሴቶች 77% የሚሆኑት **ባለፉት 3 ዓመታት የማህፀን ምርመራ ወይም የፓፕ ስሚር እንዳደረጉ** ተናግረዋል፤17% የሚሆኑት የማህፀን ምርመራ አድርገው አያውቁም፤6% የሚሆኑት ከአራት ዓመት በፊት እና ከዚያ ቀደም ምርመራ አድርገዋል።

በዳሰሳ ጥናቱ ከተሳተፉ ሴቶች 51% የሚሆኑት **የወሊድ መከላከያ ተጠቅመው እንደሚያውቁ** ተናግረዋል። የወሊድ መከላከያ ከተጠቀሙ ሴቶች መካከል 57% የሚሆኑት ባለፉት 30 ቀናት ውስጥ አንዱን ተጠቅመዋል።

ልጅ ከወለዱት ሴቶች መካከል 45% የሚሆኑት የወለዱት በቀዶ ጥገና ነው።

የግብረ ስጋ ግንኙነት እንደፈፀሙ ከተናገሩት ሴቶች መካከል 18% የሚሆኑት **የመጀመሪያ ግብረ ስጋ ግንኙነት የፈፀሙት ከ18 ዓመት በታች ሆነው ነው**፤59% ከ18-24 ነበሩ፤እና 23% 25 ወይም ከዚያ በላይ ነበሩ።

## የሴት ልጅ ግርዛት ልምድ

የሴት ልጅ ግርዛትን ማንኛውንም የሴት ልጅን ውጫዊ መራቢያ አካላቶችን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ማስወገድን ወይም ለባህላዊ፣ለሀይማኖታዊ፣እና ለህክምና ላልሆኑ ምክንያቶች በሴት ልጅ መራቢያ አካላት ላይ የሚደርስ ጉዳትንና ሂደቶችን ያጠቃልላል።[1]

**በጥናቱ ውስጥ** ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ሴቶች የሴት ልጅ ግርዛት እንዳጋጠማቸው ተናግረዋል።

**55%**
የሚሆኑት **የሴት ልጅ ግርዛት** አጋጥሟቸዋል።

**45%**
የሚሆኑት **የሴት ልጅ ግርዛት** አላጋጠማቸውም።



[1] የአለም ጤና ድርጅት፣ የተባበሩት መንግስታት የስነ ህዝብ ፈንድ እና የተባበሩት መንግስታት የህጻናት መርጃ ድርጅት (ዩኒሴፍ)። (1997). የሴት ብልት ግርዛት: መገጣጠሚያ የዓለም ጤና ድርጅት ዩኒሴፍ/UNFPA መግለጫ። የአለም ጤና ድርጅት. https://apps.who.int/iris/handle/10665/41903.

# የሴት ልጅ ግርዛት የገጠማቸው ሴቶች ልምድ

## በ ትውልድ ቦታ



የሴት ልጅ ግርዛት እንደገጠማቸው ያሳወቁ ሴቶች/በትውልድ ቦታቸው በመቶኛ:

- ሶማሊያ: 74%
- የምዕራብ አፍሪካ አገሮች [መ]: 59%
- ኤርትሪያ: 55%
- ሱዳን: 51%
- ኢትዮጵያ: 45%
- ግብጽ: 34%

[መ] የምዕራብ አፍሪካ አገሮች ቡርኪናፋሶ፣ ጋምቢያ፣ ጊኒ፣ ማሊ፣ ሞሪታኒያ እና ሴራሊዮን ይገኙበታል።

## በእድሜ

### የሴት ልጅ ግርዛት ያለባቸው ሴቶች፣ በእድሜ ቡድን

**1 ከ4 (25%)** ከ18-24 አመት ከሆናቸው ሴቶች የሴት ልጅ ግርዛት ደርሶባቸዋል።.

**ከ 43ቱ (69%)** ከ40-49 ከሆናቸው ሴቶች የሴት ልጅ ግርዛት ደርሶባቸዋል።



### ሴት ልጅ ግርዛት ካጋጠማቸው ሴቶች ውስጥ ግርዛት የተፈፀመበት እድሜ




## በሴት ልጅ ግርዛት አይነት




- **29%** የሚሆኑት የብልታቸው ክፍል **እንደተሰፋ የተናገሩ**።
- **57%** የሚሆኑት **ከብልታቸው ላይ የስጋ አካል የተወገደ** ሥጋ ተወግዷል።
- **2%** የሚሆኑት የብልታቸው ክፍል **የተቀደደ/የብልታቸው አካል ተቆርጦ ያልተወገደ**።
- **12%** በመቶዎቹ **ያጋጠሟቸውን የሴት ልጅ ግርዛት** አይነት አያውቁም።

# የሴት ልጅ ግርዛት ያለባቸው ሴቶች የጤና ስጋት

የሴት ልጅ ግርዛት ካደረጉ ሴቶች 67% የሚሆኑት ከወሊድ ጋር ተያይዞ የጤና እክል ይገጥማቸዋል ይህም ግርዛት ያላደረጉ ሴቶች ጋር ሲነፃፀር 49% ነው። ከወሊድ ጋር ተያይዘው የሚመጡት ችግሮችም ከወሊድ በኋላ ያለ የደም መፍሰስ፣በወሊድ ወቅት የሚፈጠር ሰፊ የሴት ብልት መቀደድ ወይም ድንገተኛ ቀዶ ጥገና ናቸው።

የየሴት ልጅ ግርዛት ካደረጉ ሴቶች 47% የሚሆኑት የስነ ተዋልዶ የጤና እክል ይገጥማቸዋል ይህም ግርዛት ያላደረጉ ሴቶች ጋር ሲነፃፀር 23% ነው።ይህም በወር አበባ ጊዜ ደም ለመፍሰስ አለመቻል፣ የሽንት መሽናት ችግር፣ሽንት በሚሸናበት ወቅት ህመም፣ እና የተለያዩ የሽንት ቧንቧ ኢንፌክሽኖችን ያጠቃልላል።

የሴት ልጅ ግርዛት ካደረጉ ሴቶች 44% የሚሆኑት በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት እክል ይገጥማቸዋል ይህም ግርዛት ያላደረጉ ሴቶች ጋር ሲነፃፀር 17% ነው።ይህም በወሲብ ወቅት የሚኖር መድማትንና ህመምን ይጨምራል።

የየሴት ልጅ ግርዛት ካደረጉ ሴቶች 35% የሚሆኑት ለብዙ ሳምንታት ሀዘን እንደሚሰማቸው ተናግረዋል። ይህም ግርዛት ያላደረጉ ሴቶች ጋር ሲነፃፀር 24% ነው።

## የሴት ልጅ ግርዛት ያለባቸው ሴቶች ማጽናኛ ከአቅራቢው ጋር በመነጋገር

58% **የሚሆኑት የሴት ልጅ ግርዛታቸውን** ከጤና አጠባበቅ አቅራቢ ጋር ለመወያየት ምቾት ይሰማቸዋል።



31% የሚሆኑት **የሴት ልጅ ግርዛትን** ከጤና እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ተወያይተዋል።



## የሁሉም ሴቶች የሴት ልጅ ግርዛት አመለካከት

**91%** **የሚሆኑት** የሴት ልጅ ግርዛት መቆም እንዳለበት **ያምናሉ።**

**87%** **የሚሆኑት የሴት ልጅ ግርዛት** በኋለኛው የህይወት **ዘመናቸው የጤና ችግር** **እንደሚፈጥር** ያምናሉ።

**82%** **የሚሆኑት የሴት ልጅ ግርዛት ያስፈልጋል ብለው አያምኑም** በሃይማኖት።



የ WHNS የገንዘብ ድጋፍ የተደረገው በበሽታ ቁጥጥር ማዕከላት፣ በዩኤስ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ የሴቶች ጤና ቢሮ እና የፍትህ መምሪያ፣ የፍትህ ብሔራዊ ተቋም፣ የወንጀል ሰለባዎች ቢሮ ነው።

ለበለጠ መረጃ https://www.norc.org/research/projects/a-study-of-womens-health-needs-in-the-us.html ይመልከቱ።